# ቃል

ከአለቱ

ቃል የእምነት ዕዳ ነው፣ ከቶ 'ማይታጠፍ፣
ፈታኝ አስቸጋሪ፣ የከበደ ከዶፍ፣
መሆንን የሚሻ፣ ነዶ እ'ደበራ ጧፍ።
ተከብሮ የኖረ፣ በጥቂቶች ብቻ፣
ቃል እጅግ ፈታኝ ነው፣ የሌለለት አቻ።
ደግ ነገር ያሉት፣ በቃል የሚታሰር፣
በገቢር የሚታይ፣ የፈተና ምስጢር፣
በ'ሳት የሚፈተን፣ እጹብ ፍጹም ክብር፣
ቃል ያስተዛዝባል፣ ካልታየ በተግባር።
ጥንትስ ተብሎ የለ፣ ህላዌ ነበረ፣
ከዩኒቨርስ በበፊት፣ ማልዶ የነጠረ፤
ለዚህም ይመስላል፣ ቃል ሆኖ መገኘት፣ የሰው ማንነቱ፣
ባይናችን የሚታይ፣ ህያው በድርጊቱ፤
ሲወሳ የሚኖር፣ በምሳሌነቱ፣
የተግባር መመሪያ፣ መታወቂያ እሴቱ፣
ቃል ሆኖ ተገኝ፣ የሰው ሃይማኖቱ፣
መጽናኛ መዳኛ፣ ፍቱን መድሃኒቱ።
መጽሐፍ ቅዱስን፣ ቢያንበለብሉ ባፍ፣
ወንጌልን ቢሰብኩ፣ ከጅምር እስከ ጫፍ፣
ቢያጣቅሱ ተምሳሌት፣ በቁጥር በምዕራፍ፣
ከፍጥረት ተነስተው፣ እስከወንጌል ጫፍ፣
መላዕክታት ቢጠሩ፣
ነብዮች ቢቆጠሩ፣
ቢለፍፉ ዲስኩር፣ ሁሩ ከምህገሩ፣
በ'የሱስ ቢምሉ፣
ቢደፉ ከመስቀሉ፣
ምንም ፋይዳ የለው፣ ሳይገኙ በቃሉ፣
ቀን እየመሰሉ፣
ማታ ማታለሉ።
ትርፉ ኩነኔ ነው፣ በቁም የሚያቃጥል፣
እንደ ሰደድ እሳት፣ ለብልቦ እሚገድል፣
ሰው የሚለውን ስም፣ አሽቀንጥሮ የሚያስጥል።
በእውነት ምድረ በዳ፣
ዜማ ቢንቆረቆር፣
ቅኔ ቢደረደር፣
ወንጌልም ቢሰበክ፣ ቢቀራ ቁርአን፣
ያንድዬን ስም ጠርተው፣ ቢያዜሙ ቢሰግዱ፣
በማህሌት ቢያረግዱ፣
የስራኤልን ጌታ፣ ስሙን እየጠሩ፣ በሰፊው አዳራሽ፣ በስሜት ቢነጉዱ፣
ቃል ካልታከለበት፣ እንደው በከንቱ ነው፣

ነጭ ውሸት ብቻ፣ እርባና የሌለው።
ስለዚህም ሰዎች፣ ቃል የእምነት ዕዳ ነው፣
ቀን እየሰበኩ፣ ማታ የማንክደው።
መሆኑን ካወቅን፣
ያስፈልጋል ብጹዕ፣ ለቃሉ ያደረ፣
አርአያ የሆነን፣ ማተብ የቋጠረ!
ያስፍልጋል ብጹዕ፣ ያስፈልጋል ጀግና፣
ቃሉን የሚያከብር፣ የእውነት ደብተራ፣
ህያው እንዳበበ፣ በቃሉ የኖረ፣ ከሰማዕታት ጋራ፣
የነፃነት ጸጋ፣ የእምቢተኞች አውራ።

አዎ!

ያስፈልጋል ብጹዕ፣ ለቃሉ ያደረ፣
አርአያ የሆነን፣ ማተብ የቋጠረ!
ያስፍልጋል ብጹዕ፣ ያስፈልጋል ጀግና፣
ቃሉን የሚያከብር፣ የእውነት ደብተራ፣
ህያው እንዳበበ፣ በቃሉ የኖረ፣ ከሰማዕታት ጋራ፣
የነፃነት ጸጋ፣ የእምቢተኞች አውራ።

(12/02/2003)